# ከ ዜ ና ው  ባ ሻ ገ ር

*መስፍን ታምራት (ከናይሮቢ)*

(*ሐዋርያ ቅጽ* 11፤ *ቁ.* 6፥ *ሐምሌ* 1998 *ዓ.ም* )

ተለዋዋጩ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሁኔታ ወደፊት ሄደ ሲሉት ወደኋላ፤ ሰመረ ሲሉት ሿ ብትን፤ አለፈልን ልንል ስንቃጣ ወቸ ጉድ ገና መቸ ጉዱ አልቆ እያለ ወደ ቀቢፀ ተስፋ ሊከተን በመጣር ላይ ነው። ግን ይህም ያልፋል።

ህባሪ ጋኒ። በሰሞኑ ኦነግ የውይይት ርዕስ ሆኗልናም አካም ጂርታ።

ኢትዮጵያ በብሄረሰቦች የእርስ በርስ ግጭት እንድትታመስ ወያኔ ያጠነጠነው ሴራ በዚህ ወረ በተለይ በልዩ ልዩ ቦታዎች ተከስቶ ለብዙ ህይወት ማለቅ ምክንያት ሆኗል። ኦሮሚያና ሶማሌ ክልል በተባሉት በተለይ ብዙ ጉዳት ደርሷል፤ በሰሞኑ በቦረናና ጉጂ ህዝብ መሀል በተከሰተ ግጭት ከ150 ያላነሰ ዜጋ ህይወቱን አጥቷል። በጂጂጋም የሃይማኖት ግጭት ተቆስቁሶ የፁህን ህይወት ጠፍቷል። የመለስ አገዛዝ ወደ ውድቀቱ ሲያመራ ይሁነኝ ብሎ ህዝብን በማናከስና በማዋጋት ቀውሱን ለመሸፈን ወይም የሕዝብን ትኩረት ወደ ሌላ አቅጣጫ ለመሳብ እየሞከረ ነው። በአጠቃላይ ግን በዚህም በዚያም ብልጭ ድርግም እያለ ያለው ግጭትና ጦርነት ባለበት ከቀጠለ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አዳጋች አይደለም። አገዛዙ ጊዜ እየገዛ ከበረከተም በሀገሪቷ ላይ የሚደርሰው ቀውስ በቀላሉ የሚገመት አለመሆኑ ግልፅ ነው።

ምንም እንኳን ድርጅቶች ራሳቸውን ተቃዋሚ ስላሉ ተቃዋሚ ናቸው ባይባልም፥ የተቃዋሚ ድርጅቶች ህብረት መኖሩ ለድል ጠቃሚ ነው ተብሎ በተደጋገሚ ተነግሯል። በአንድ ወቅት "ተባበሩ ወይም ተሰባባሩ" ብሏል ህዝቡም ተብሎ ነበር (በነገራችን ላይ ይሄን ይደጋግም የነበረው ግለሰብ ዛሬ ከወያኔ አብሯል)። ይህን በመቀበል ደግሞ ተቃዋሚ ድርጅቶች ሊያብሩ ሲሞክሩ የተሸረበውን ሴራ፥ የነበረውን ጋሬጣ የምናስታውሰው ነው። የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት /ኢዴኃህ/ን ለመመስረት ቢያንስ ሁለት ዓመት ፈጅቷል። ህብረቱ በተመሠረተ ማግስትም ሁለት ድርጅቶች ተቀስቅሰውና ተቆስቁሰው ከህብረቱ ወጡ። ቆስቋሾቹ ዛሬም በዚሁ አፍራሽ ሚናቸው ንዋይን ተገን አድርገው የሚጓዙት ሲሆኑ፥ ሁለቱን እናዋህዳለን ብለው የሞከሩትም መሳቂያ መሳለቂያ ሆኖ ቀረ። የዚሁ ውህደት አንድ አካል ይሆናል ተብሎ የነበረው ቡድን ደግሞ ሲመሰረት ጀምሮ እትብቱ ከወያኔ ጋር የተያያዘ መሆኑ በይፋ ቢነገርም ይህ ማስጠንቀቂያ በአሉታዊ ተወስዶ በተለይ በሐዋርያና በኢሕአፓ ላይ የተደረገው የማጥላላት ዘመቻ የሚታወስ ነው። የዚህ አምድ ፀሀፊ በሚያውቀው ግን በደርግም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የመንግስት ሰላዮች ተደብድበው ሳይቀር በእስር ቤት ተወርውረው የሸፋን ታሪክ እንደሚያዘጋጁ የታወቀ ጉዳይ በመሆኑ፥ የእገሌ "ታስሮ ነበር" ለሀገር ወዳድነት ሰርቲፊኬት ወይም ማረጋገጫ አለመሆኑን ያውቃል። ይህ የትላንቱ ሀቅ ለዛሬም ማመዛዘኛ የሚጠቅም መሆኑም ግልፅ ነው።

በሀቅ ለሀገር ሲባል ሊመሰረት የሚገባው ሰፊ ግንባር እውን አለመሆኑ የሕዝቡን ትግል እየጎዳው ሄዶ በተለይም ደግሞ የተወሰኑት የተቃዋሚ ድርጅት አባላት ደግሞ ሕዝብን ብቻ ሳይሆን የትግል ጓደኞቻቸውንም ከድተውና አሳልፈው ሰጥተው ከመለስ ጎን ሲሰለፉ፥ በሕዝባዊ ትግሉ ሂደት ላይ ያደረሰው ጉዳት ከባድ ነበር። ከዚህ ጋር ተያይዞ ደግሞ ድርጅታዊ ትምክህት ቀና ቀና በማለቱ ህብረት ሲጠራ አጓጉል ልመና የመሰላቸውም የዘመኑ ፖለቲከኞችም ነበሩ። በታሪካችን ሙጃ ድርጅቶች፤ ብቅ ብቅ ብለው ፀሐይ ሲወጣ ወዲያው የሚጠወልጉ ያየን በመሆኑ የ"ወጣ ወጣና እንደ ሽንበቆ" ተመክሮን ዛሬ መርሳቱ ይከብደናል። ሆኖም ለሁሉም ጊዜ አለውና ጊዜ ራሱ ያስተምራል በሚል የተውነው ጉዳይ

በጠራራ ፀሐይ ሆኗል። ሐዋርያ ጋዜጣ ከወያኔ ያልተደበቀውንና ከህዝብ ግን የተሰወረውን በማውጣት ደረጃ ሚናዋን ስትጫወት፥ ህብረትን አስመልክቶ ደግሞ በሀቅ የሚጥረውንም ያበየውንም ወይም እምቢ ያለውንም በጅምላ አልወቀሰችም። የቄሳርን ለቄሳር ሰጥታለች። ይህ አልዋጥ ያላቸው ያው ትላንትም ዛሬም በሐዋርያም ላይ መዝመታቸው የሚጠበቅ ነው።

ይህን መንደርደርያ ካቀረብን በኋላ ደግሞ ወደ አዲሱ ክስተት ማለትም "ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ" ተብሎ የተሰየመውን ስብስብና ያስከተለውንም ውዝግብ ማንሳት የግድ ይሆናል። የትብብሩን/አልያንስ/ ይዘት ለመረዳትና ለምንስ ኢዴኃህና ሌሎች ተቃወሙት ለሚለው መልስ ለመስጠት ደግሞ እስከተቻለን ድረስ ወደኋላ ሄድ ብለን ስለ ምስረታው ሂደትና ከዚያም ስል ስብሰባውና ሰነዱ፣ ስለ ተካፋዮ -፥ ወዘተ ማንሳት አለብን። ይህ ሁሉ ደግሞ አሁንም ተደብቆ ቆይቶ የሚወጣ ምስጢር ሳይሆን በሰነድ ደረጃ የሰፈረና በዚህም በዚያም መድረክና ራዲዮ ለሕዝብ ግልፅ የተደረገ ነው። ስለዚህም ወደ ሐዋርያ ጣት ቅስራ የለመደባቸው አደብ ይግዙ ብለን ወደ ዝርዝሩ እንሄዳለን።

ሁሉን አቀፍ የተቃዋሚ ድርጅቶች ጉባዔ የሚለውን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አቅዋም አድርጎ ያስተጋባው ህብረቱ ነው። ከሁለተኛው ጉባዔው በኋላም ይህን ጉባዔ የሚያዘጋጅ ግብረ ኃይል ይቋቋም በሚል ጥሪ አሰምቶ ለየድርጅቶቹም ደብዳቤ ፅፎ ነበር። ለዚህ ጥሪ ኦነግ በፅሁፍ አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጥ ቅንጅቱ በሻለቃ ዮሴፍ በተፈረመ ደብዳቤ አማካይነት ለዚህ ዓይነቱ ስብሰባ "ጊዜውም ውክልናውም" እንደሌለው ገልጿል። በኦነግና በህብረቱ መሀል ሰፋ ያለ ውይይት እየተካሄደ ባለበትና ኦነግ በኢትዮጵያ አንድነት ክልል የመብት ጥያቄውን ሁሉ እንዲያስተናግድ ግፊት እየተደረገ እያለ የቅንጅት የሰሜን አሜሪካ መሪዎች፣ ራሱ አቶ ሰለሞን በቀለ እንዳለው- በዱባይ ከኦነግም ከሻዕቢያም ሲገናኙ፥ በኦነግ በኩል ሁናቴው ተለወጠ። እንደ ጦር ይፈራው የነበረውን ቅንጅት በአቶ ሰለሞን በቀለ፣ ዶክተር ስዩም ሰለሞንና ሻለቃ ዮሴፍ አማካይነት ኦነግ ሲያገኝ ትልቁ ዳቦ ሊጥ ሆኖበት በፈለገው ሊያሰኬዳቸው የሚችል መሆኑን ሲረዳ፥ ከህብረቱ ጋር የጀመረውን ድርድር አቆመ፣ አቋረጠ። አቶ ዳውድ ኢብሳና የኦነጉ የውጭ ጉዳት ሀላፊ አቶ ሀሰን ሁሴን ሆኑ የሻዕቢያው ተጠሪ (አዋቴ ድህረ ገፅ አቶ የማነአብ ነበር ያለው) ከእነ አቶ ሰለሞን ሲነፃፃሩ በፖለቲካ ችሎታ ሰማይና መሬት ሆነው መገኘታቸው አስገራሚም አልሆነም። የቅንጅቱ ቡድን ኦነግን "ህብረትን አትጥሩ" ብሎ መማፀኑንም ለማወቅ ተችሏል። ህብረት በኢትዮጵያ አንድነት ከሚያምኑ የብሄረሰብ ቡድኖች ጋር መስራቱ አልዋጥ ያለውና የተቃወመ ቅንጅት ኢትዮጵያዊ አይደለንም ከሚሉ የብሄረሰብ ድርጅቶች ጋር ከመቸው ገጠመ የሚለው ጥያቄ እንዴትስ ኤርትራን ሌላ ሀገር ብሎም አፀደቅ ከሚለው ጋር ተያይዞ መነሳቱ አልቀረም።

ወደ ሂደቱ ስንመለስ ደግሞ ኦነግና ቅንጅት/ከላይ የተጠቀሱት ሶስት የቅንጅት መሪዎች ነን የሚሉት በጀርመን ሀገር በፍራንክፈርት ተገናኙና ኦነግ በዚህ ጊዜ አዘጋጅቶ ያመጣቸውን ሁለት ሰነዶች ሰጣቸው። የዚህን ሰነድ ይዘት ወደ ታች የምንመለስበት ሲሆን የቅንጅቱ መሪዎች ሰነዱን አፀደቁ ። በጉባዔውም ላይ የሚገኙት ሌሎች ድርጅቶች የኦጋዴኑ ነፃ አውጪ ግንባር፣ የሲዳማ ነፃ ውጪ ግንባርና በኤርትራ ያለውና በአበሩ አታላይ የሚመራው የኢትዮጵያ አርበኞች ግንባር መሆኑንም ቅንጅቶቹ ተነገራቸው። ይህንንም ተቀበሉ። እነዚህ ድርጅቶ ቀደም ሲል ከኦነግ ጋር ግንባር መስርተው የነበሩ መሆናቸውና አሁን ተዘርዝረው ሲመጡ ቅንጅትን ሁሌም አራት ለአንድ በድምፅ እንደሚያሸንፉት ከአሜሪካ ለመጡት ፖለቲከኞቹ ግልፅ አልሆነላቸውም። የኦነግ መሪዎች የስብሰባው ቦታ ዩትሬህት ሆላንድ መሆኑንም አስታወቁ። ቅንጅቶቹ ተስማሙ። ለቅንጅቱ መሪዎች ዋናው ትኩረት ከኦነግና ሌሎችም ተስማምቶ ህብረትን ማግለሉ በመሆኑ የሀገር ጥቅም ሲጎዳ ጉዳያቸው ሆኖ አልተገኘም። ስብሰባው ሳምንት ያህል ሲቀረው የኦነግ መሪዎች አሜሪካ መጥተን በስፋት እንወያያለን ያሉትን ህብረት በሳምንት ለዩትሬህት ስብሰባ እንድትገኙ ብለው ጋበዙት። አንደሚጠበቀውም ህብረቱ በዚህ አልተስማማም።

ጉዳዩን በጥሞና ለሚያየው ኦነግ ከህብረት ቅንጅትን መምረጡ በመሰረቱ የተሳሳተ ቢመስልም፥ በጠባቡ ለሚያዩት የኦነግ መሪዎች ግን እንደፈለጉት እሺ የሚሏቸውን የቅንጅት መሪዎች በመያዝ አንሰራራ ብለው የሚፈሩትን አማራ በቁጥጥር ስር ማስገባት

መስሎ ታያቸው። ህብረቱ በሁሉም ነጥቦች ላይ በቅድሚያ እንወያይ እንስማማ ባይ ነበርና ለኦነግ መጎርበጡ አልቀረም። መረዳት እንደተቻለው ህብረቱ በግልፅ ያስቀመጣቸው የሂደት ነጥቦችና ደረጃዎች ነበሩ። እኒዘህም (1) የሚደረገው ጉባዔ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች ጉባዔ መሆን እንዳለበት (2) ሁሉም ኢትዮጵያዊ ድርጅት የሚገኝበት መሆን እንዳለበት (3) ሰነዶች በጋራ መሰናዳት እንዳለባቸው (4) የብዙሀንና ሲቪክ ድርጅቶችም መገኘት እንዳለባቸው (5) ኦነግ ግንባሩን ዘርዝሮ መጥቶ አራት ድምፅ የሚይዝ ከሆነ ቅንጅትና ህብረትም ተመጣጣኝ ድምፅ ሊኖራቸው እንደሚገባ (6) የውክልና ቁጥርና የስብሰባ ቦታም በጋራ እንዲወሰን ወዘተ የሚሉ ነበሩ። ዋናው ነጥብ ግን ይህ ጉባዔ ዓላማው ከወያኔ ጋር ሥልጣን ለመጋራት ሳይሆን በትግል የኢትዮጵያን የሽግግር መንግስት ለማቋቋም የሚነሱ ድርጅቶችን ለማስተባበር ነበር። በመሆኑም ህብረቱ ና ተሰብሰብ፣ ያዘጋጀነው ቤት ግባ ሲባል ይህን የኦነግ የእምነት ማጉደል ታዝቦና ተቃውሞ ስብሰባው አጠራሩ የተሳሳተ ነውና አሁንም አርሞ ለመጓዝ ይህ ብዙ ወጪ ተደርጎበታል የተባለ ዝግጅት በቅድመ ጉባዔ ደረጃ ይካሄድ ብሎ ሀሳብ አቅርቦ ከመቅረት መካፈሉ ይሻላል ብሎ ወስኖ በቅድመ ጉባዔ ደረጃ ተሳትፎ ለማድረግ ሲል ዩትሬህት ልዑኮች ላከ። በስብሰባው ሲገኝ ደግሞ ሁሉም ጉዳይ ተጠናቆና አልቆ በቀድሞ የምስራቅ አውሮጳ ኮሙኒስተ ፓርቲዎችና በህወሓት ጉባዔዎች እንደታየው ጉባዔው ለይስሙላ መሆኑ ተጋለጠ። አቶ ዳውድ ኢብሳ ማንም ሳይመርጠው ራሱን የስብሰባው ሊቀ መንበር ብሎ ለሶስት ቀን ተሰየመ። የኦነግ ሁለት ሰነዶች- የስምምነት መርሆዎች/ሜሞራንደም ኦፍ አንደርስታንዲንግ/ እና ህጎች/ስታትዩትስ/፣ ለህብረቱ ልዑክ ቡድን ተሰጥተው በሰዓት ተኩል ምላሽ ተጠየቁ። በአጠቃላይ ይህ በቅንጅት መሪዎች አሳዛኝ ተባባሪነት የተካሄደ የኦነግ ቧልት ህብረቱን ሊያደናግር ባለመቻሉ ተመሰረተ በተባለው ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ህብረቱ አባል አልሆንም ብሎ ቀረ። እስከዛሬ በይፋ ባይነገርም አቶ ዳውድ ኢብሳ የትብብሩ ሊቀመንበር፣ ቅንጅት ምክትል ሊቀመንበር፣ አቶ ሃሰን የኦነጉ የትብብሩ ውጭ ጉዳይ ሀላፊ፣ በዚያድ ባሬ የቀድሞ ባህር ኃይል አድሚራል ወይም አለቃ የሚመራው የኦጋዴን ግንባር ደግሞ ፀሃፊ ሆነዋል። በዚህም ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቅንጅት ሶስት ለአንድ መሆኑ ቢያንስ እነ አቶ ሰለሞንን ያሳሳበ ጉዳይ አልሆነም። ትብብሩ በተቋቋመ ማታ የኤርትራ ቴሌቪዥን ከምስል ጋር የትብብሩን መቋቋም ለኢትዮጵያ አስተላልፏል።

ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ:- በምስረታው ጉባዔ ምን ጉድ ታየ? መሰረታዊ የአቅዋምና የመርህ ይዘቱ ምንድነው? በአሁኑ ጊዜ ለእነዚህ ጥያቄዎች ግልፅ ምላሽ መስጠት ሲገባ ሰነዶቹን የፈረሙት የቅንጅት ተጠሪዎች በየራዲዮኑ የሀሰት "መረጃ" እየሰጡ ናቸው።

- ለምሳሌ አቶ ሰለሞን በቀለ ስብሰባው የተካሄደው በአማርኛ ነው ብለው ዋሽተዋል። ምንም እንኳን ከኦጋዴኑ ተወካይ ሌላ ሁሉም አማርኛ ቢናገሩም ስብስባው የተካሄደው ሆን ተብሎ በባዕድ ቋንቋ መበእንገሊዝኛ ነበረ። የትብብሩ የመጀመሪያ ቋንቋ እንግሊዝኛ ይሆናል መባሉና ይህም በእነ አቶ ሰለሞን መደገፉ የሚካድ አይደለም።

- በግንባሩ ስም ኢትዮጵያ የሚል አለመኖሩ ዶክተር ስዩም እንደሚያስረዳው "ቅንጅትም ኢትዮጵያ የሚል በስሙ የለም ዓይነት" ጉዳይ ሳይሆን ኦነግና የኦጋዴነ ግንባር የህበሻ ቅኝ ገዢነትን የምንዋጋ ኢትዮጵያዊ ያልሆን ነን ስለሚሉ ለእነሱ እንደሚስማማ ተደርጎ ነው፡ ይህን ቅንጅት መሪ ነን የሚሉት የራሱ የቅንጅትን ማኒፌስቶ ወይም ፕሮግራም ተፃረው እንዴት ተቀበሉ? አፀደቁ?

- በስብሰባው ሂደት የሌላ እጅ ጣልቃ ገብነት በስልክ ልውውጥና ወጥቶም በመመካከር ጊዜ የታየ ነው።

- ትብብር ለነፃነት የተባለው የኦሮሚያና ኦጋዴኒያን ነፃነት እንፈልጋለን ለሚሉት በሚያመች ሁኔታው መሆኑ ግልፅ ነው።

- የወያኔን ህግ መንግስት እንቀበላላን ማለት ብቻ ሳይሆን ወደፊት የሽግግር መንግስት ሲቋቋምም ይኸው የወያኔ ህገ መንግስት የሚሰራ ይሆናል (ወያኔ በሽግግሩ ወቅት የደርግን

ህገ መንግስት የጠበቀ  ይመስል!) መባሉ ለእነ ኦነግ አንቀፅ 39 ለመጠበቅ ታቅዶ መሆኑ ግልፅ ሆኖ ሳለ የቅንጅት መሪዎች ግን ይህን ተቀብለው አፅድቀዋል፡፡

• የቅንጅት አመራርና አባላት ሁሉ (የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ አናንሳና!) ሳይመክርበትና አቅዋሚ ሳይለው በሆላንድ ስብሰባ የተገኙት የቅንጅት መሪዎች ኤርትራን እውቅና መስጠታቸው ደግሞ ሌላ ከባድ ስህተት መሆኑ አላጠራጠረም፡፡

ከሚነገረውና ለማደናገር ከሚወረወረው ባሻገር ትብብሩ በመጀመሪያ ደረጃ መዳኘት ያለበት በመርሁና አቅዋሙ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ሲታይ ኦነግን ወደ ኢትዮጵያ ቅንጅት የሳበው ሳይሆን በአነ ሰለሞን-ስዩም አማካኝነት ኦነግ የልቡን አድርሶ ቅንጅትን በስሩ ማድረጉን ማየት ይቻላል፡፡ ህብረቱ ለምን እምቢ እንዳለ አቅዋሙን በመግለጫዎች አውጥቶ አሳይቷል፡፡ ትብብሩ ስለ ህብረቱ አቅዋም የተሳሳተ መግለጫ እየሰጠ ስለነበርም ህብረቱ በጊዜ ለአባላቱ፣ ለደጋፊዎቹና ለህዝብ አቅዋሙን ግልፅ ማድረጉ ለትግላችን በጣም ረድቷል፡፡ አቶ ዳውድ ኢብሳ ወይም ኦነግ የቀየረው ምንም አቅዋም እንደሌለ በዋሺንግተን ዲሲ ንጋት የተባለ ራዲዮ ላይ ኢትዮጵያዊ ነን ትላላችሁ ወይ ተብሎ አራት ጊዜ ሲጠየቅ አራት ጊዜም ጥርት ባለ መንገድ አልመልስም ማለቱ በቂ ምስከር ነው፡፡ ኢትዮጵያዊ አይደለንም የሚሉ ግንባሮች ከኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋር በስብሰባ መቀመጣቸው በራሱ ብቻ ብዙ ሚዛን ያለው ጉዳይ አይደለም፡፡ በዚህ መንገድ ለግንጠላው አላማቸው ይጠቅማል ብለው ከሆነ ስብሰባው የሚካሄደው ምንም ለውጥን ተንተርሶ አይደለም፡፡ ኦነግ ቅንጅትን፣ በከተማው አነጋገር “ ሸወደው” እንጂ የኢትዮጵያ ትግል አጋሩ አልሆነለትም ቢባል ስህተት አይሆንም፡፡ በሰነዶቹ መሰረት ትብብሩን ማወቅ ሲባልም ዛሬ ጉዳዩን ህብረቱን ወይም የፈረደበትን ኢሕአፓን በአፍራሽነት በመወንጀል ሳይሆን በተፈረመው ሰነድ መሰረት/ለምን ተተርጉሞ አልቀረበም ለህዝብ?/ መመርመር ያለበት ነው፡፡ የዚህም ወሳኝነት ባለፈው ወያኔ ኢሕአዴግ-ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ያደረሰውን ጉዳት የሚያይ ነው፡፡ የአሁኑ የሚብሰው ደግሞ ከብሄረሰብ ድርጅቶች ጋር አልሰምርም ሲል የቆየው ቅንጅት አቅዋሙን ቀይሮ ያውም ኢትዮጵያዊ አይደለንም ከሚሉት ጋር ትብብር መፍጠሩ ብቻ ሳይሆን ተባባሪዎቹ እርማችሁን አውጡ ኢትዮጵያዊ አይደለንም፣ አንሆንም የሚሉ መሆናቸው ነው፡፡ የዚህ አምድ ፀሃፊ “የረቀቀው” የእነ ሰለሞን በቀለ ፖለቲካ ሊገባው ያልቻለ ይሆናል ብንልም እንኳን የቅንጅቱ ሰከን ያሉና ህጋዊ መሪዎች ከዚህ ትብብር ርቀው ኢትዮጵያን ባስቀደመ መንገድ በሌላ ሁሉን አቀፍ ጉባዔ ዝግጅት ከኢትዮጵያዊ ድርጅቶች ጋር ቢተባባሩ የሚሻል መሆኑ የሚካድ አይደለም፡፡

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የቀመመው ሳይሆን በይዘቱና አፋን ኦሮሚፋ ደረጃም በቃናው የኦነግ የሆነው ሰነድ ይህ ድርጅት ለምን ከ“ሀበሾች” ጋር ትብብር ለማድረገና በዚህም ነፃ ኦሮሚያን ለማቋቋም ዕቅድ እንዳለው በግልፅ ተቀምጧል፡፡ በፖለቲካ ድርጅትነት ደረጃ ተቃዋሚዎችን አማራ፣ ኦሮሞ ወዘተ በሚል ብቻ የሚገመግመው ኦነግ ቢያንስ የቅንጅት መሪዎች ነን ብለው ከተገናኙት በተሻለ የሚፈልገውን የሚያውቅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ በባዕዳን እርዳታ ከወያኔ ጋር ተደራድሮ ስልጣን ለመቀራመት ኦነግ የተገደደበት ዋናው ሁኔታ በሀገራችን ተጨባጭ ፖለቲካ ቦታ እያጣ በመምጣቱ ነው፡፡ በሻዕቢያ ተደግፎ የጀመረው የትጥቅ ትግል ወያኔን የሚያሰጋ ሊሆን አልቻለም፣ አልሆነለትም፡፡ ባለፈው የግንቦት 97 ምርጫ ደግሞ ቅንንጅት በመጀመሪያ ደረጃ ከዚያም የኦሮሞ ብሄራዊ ኮንግሬስና የአቶ ቡልቻ ደመቅሳ ቡድን የኦሮሞን ህዝብ ድምፅ አግኝተዋል፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ኦነግን አዳምጦና ባዕድ ነኝ ብሎ እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም፡፡ በኢትዮጵያዊነት ለኢትዮጵያ ሲል በኢትዮጵያ ለሚያምኑ ድርጅቶች ድምፅ ሰጥቷል፡፡ ኦነግ የሩቅ ተመልካች ሆኖ በመገኘቱ በአንድ በኩል ከእነ መረራና ቡልቻ ጋር  በምስጢር ለማበር ሲጥር በሌላ በኩል ደግሞ ከወያኔ ጋር ተስማምቶ “የአማራ ማንሰራራት” የሚለውን ለማደናቀፍ አቅዶ ተንቀሳቅሷል፡፡ በጣም የሚያስገርመው ግን የትብብሩ ሰነድ ላይ ስለ ግንቦቱ 97 ምርጫ /የሕዝብ ድምፅ ይከበር ከሚለውም አንፃር/ ምንም የተባለ አለመኖሩና የምርጫው ዋና አሸናፊ ድርጅት የቅንንጀቱ መሪዎች ነን ያሉት ግለሰቦችም ይህንኑ መቀበላ  ው ነው፡፡ ጆሮ እያደር ጉድ ይሰማል ነው ነገሩ፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ደግሞ የፖለቲካ ነጋዴዎቹ በየፊናቸው እየተንቀሳቀሱ ነው:: መሰረተ ቢስ የጦርነት መግለጫዎች ከዚህም ከዚያም ይበራሉ:: ቋራን ወረዳ ወደ ጎጃም ይከቱታል፣ የቋራን ጦር ሰፈር መታን ሲሉ ቋራ ወረዳ መሆኑንም ሰው አያውቅብንም ያሉ ይመስላሉ:: በቦታው በከባድ ሁኔታ ሊታገሉ የሚሞክሩት ሌላ ሆነው ሳለ ሌሎች መግለጫ ያወጣሉ:: ጦር ሜዳ ነን ብለው በስልክ ሰብሰባ የሚያናግሩም ብቅ ብለዋል:: ዜጋው በብዛት ግን ከገንዘቡ ለመለያየት የተቻኮለ ይመስላል:: ከግማሽ ሚሊዮን ዶላር በላይ ለአማላጅ ተቋም (ሎቢ ፈርም) የከፈለው የሰሜን አሜሪካ ቅንጅት ለቀድሞው የኒው ዮርኩ ከንቲባም ለዚሁ ስራ በወር 40 ሺ ዶላር/ 360 ሺብር/ እየከፈለ ነው:: ይህ እንግዲህ የድርጅቱ መሪ አቶ ብርሃኑ መዋ በየወሩ ይከፈላቸዋል ከሚባለው 5 ሺ ዶላር/45 ሺ ብር/ ከሚለው የሚደመር ነው:: ጦር አለን ገንዘብ አምጡውን ዜጎች በቀና ልብና በእምነት በመውሰዳቸው እየተዘረፉ ነውና ይህ መታወቅ አለበት:: ይህ ግን ማስጠንቀቂያው እነሆ ተላልፏል:: እንደ ኮለኔል ጎሹ "ጦር" ጊዜ፣ እንደ ልደቱ ጊዜ ለሀቅ ጆሮ ካልተሰጠ አልሰማም ያለው መቸገሩ የማይቀር ይሆናል:: በበኩላችን ሃቁን ተናግረን ሕዝብ ለውሳኔ ይበቃ ዘንድ ሃላፊነታችን ተወጠናል:: ነገ ላለመቆጨትና ላለማፈር ዛሬ በስሙ ለሚመከርለት የኢትዮጵያ ሕዝብ የምናውቀውን በድፍረት ግልፅ አድርገን ከመሸበት ማድርን መርጠናል:: በዚህ ጸሃፊም ሆነ በሐዋርያ ላይ እንደተለመደው ሊከተል የሚችለውን ጊዜያዊ የጥቂቶች አላዋቂና ግብዝ ትችት÷ እንደዚሁም 'እንዴት ተነክተን' ከሚሉትና ምክንያት ፈልገው ሊረባረቡ ከሚፈልጉት ጎራ የሚሰነዘርብንን ሁሉ እንዳመጣጡ ለመቀበል ዝግጁ ነን፣ የጋዜጣዋ አንባቢዎችና ወዳጆችም በዚህ በኩል ነቅታችሁ ትጠብቁ ዘንድ እናሳስባለን፣ ይህ ስለእውነት ዘብ የመቆምና የሀገር ህልውና ጉዳይ ነው::

እስቲ ሌሎች ዜናዎችን እንያቸው

• በሚቹ ኢንጂነር ቅጣው ተቋቋመ ከተባለው ቡድን ጋር ተዋህድኩ ያሉት ኮለኔል አስራት ከቡድኑ ተጣልተው ተለያይተዋል:: ሁለቱም ወገኖች መግለጫ አውጥተዋል:: ሆኖም ኢነፍ የተባለው የድህረ ገፅ ራዲዮ በኮለኔሉ እጅ እንዲገባ የራዲዮው ደጋፊዎች/ከአትላንታና ሎስ አንጀለስ/ወስነዋል ተብሏል:: የኢንጂነር ቅጣው ቡድን መሪ የነበሩት ዶክተር በቀለና የካናዳው መላኩ ደግሞ በራሳቸው ሊቀጥሉ ተዘጋጅተዋል የሚል ዘገባ አለ::

• በጋምቤላ የሚንቀሳቀሱ የአኝዋክ ታጣቂዎች የወያኔን ሰላም አውቶቡስ ላይ ደፈጣ አድርገው 30 ያህል የሚሆኑ (በአብዛኛው የወያኔ ካድሬዎችን ተብሏል) ገድለዋል::

• በገሬና ቦረና መሀል በተነሳው ግጭት ከ 150 በላይ ሰው መገደሉ የተዘገበ ሲሆን ወያኔ የብሄረሰብና የሀይማኖት ግጭቶችን እያፋፈመ መሆኑ ተረጋግጧል::

• በጅጅጋ ያለውን የቤንዚን ከምችት ወያኔ ወደ ጅቡቲ ወስዶ መሸጡም ተጋልጧል::

• የመለስ ዜናዊ የመጠጥና የጫት ጓደኛ የነበረውና በአሜሪካ አምባሳደር ተብሎ የተሾመው ሳሙዔል አሰፋ በየማታው ዋሽንግተን ዲሲ መሸታ ቤቶች መስከር በመጀመሩ ከወደ አዲስ አበባ ግሳፄ ሊላክለት ነው ተብሏል:: በረባ ዜና ደረጃ ግን በኤምባሲው ያሉት አዲስ ሹሞች ኢትዮጵያውያንን ለማግባባትና በወያኔ ዙሪያ

በኢሕአፓ ላይ የሀሰት ክሶችን በወያኔ ራዲዮኖች ለሰዓታት ማሰማትን ቀጥለዋል::

• በቅርቡ የተቋቋመውን ትብብር አስመልክቶ ፈራሚዎቹ የቅንጅት መሪዎች ከኦነግ ጋር ግንኙነትን ከመሰረትን ቢያንስ ሶስት ዓመት አልፏል ያሉት በቃሊቲ ላሉት የድርጅቱ መሪዎች ጎጂ ነው ተብሏል:: ወያኔ መሪዎቹን ከኦነግና ሻዕቢያ ተባብረው ሽብር ሊፈጥሩ ነበር ብሎ በሀሰት እየከሰሰ ሳለ ይህ የቆየ ግንኙነት ነበረን የሚለው ንግግር ሃላፊነት የጎደለው ነው ተብሏል::

• በሶማሊያ ወያኔ የሚደግፈው ስብስብ ተሸንፎ አል ኢቲሀድ አል ኢስላሚያ የተባለው ቡድን አባል የሆነበት የእስላም ፍርድ ቤቶች ህብረት በአሸናፊነት ወጥቶ ሞቃዲሾንም

ጆውሀረንም መያዙ ለመለስ ዜናዊ መርዶ ነው ተብሏል፡፡ አል ቃይዳ የተባለው ቡድን በሶማሊያ መሽጓል ብሎ አሜሪካንንም ያሳመነው ወያኔ ሲረዳቸው የነበሩ የጦር አበጋዞች መሸነፋቸውም አሜሪካንንም ያስደነገጠ ክስተት ሆኗል፡፡

• ሌላ የደረሰን ዜና ደግሞ ቅንጅትና ኦነግ የጋምቤላ ህዝብ የተበባረ ዴሞክራሲያዊ ግንባርን ከህብረቱ ወጥቶ ከትብብሩ እንዲገባ ለማድረግ አነጋግረውት የህብረት አባል የሆነው የጋምቤላ ግንባር ይህን አግባብ የለሽ ስራ አልቀበልም ማለቱ ተዘግቧል፡፡ በዚህ አልሳካ ሲላቸው ለትብብሩ ተለጣፊ የሆነ የጋምቤላ "ግንባር" በአንድ የቅንጅት ደጋፊ አማካይነት ሊመሰርቱ መሆናቸውም ተደምጧል ከወያኔ ትምህርት ይሏል ይህ ነው!የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሰላምን አጥቷል፡፡ ሱዳንን በእጅ አዙር የሚያምሰው የሻዕቢያ መሪ ሱዳን ሄዶ ግንኙትን ሊያሻሽል እየሞከረ ነው፡፡ ሱዳን በዳርፉር ግዛቷ መታመሷን ቀጥላለች፤ ባዕዳንም በሰፊው ጣልቃ እየገቡ ነው፡፡ ነገ የተሻለ ሁኔታን የሚያመጣ መስሎ አይታይም፡፡ በራሳችን ሀገር የተሻለ ሁኔታን ለማምጣትና ለወያኔ ጊዜን ላለመስጠት ትግላችን ይፋፋም እያልኩ እስከሚቀጥለው ልሰናበት፡፡